# የብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄና ፈተናዎቹ በኢትዮጵያ

*በዳዊት ተሾመ*

## 1. መግቢያ

ከደርግ የ17 አመታት የአገዛዝ ውደቀት በኋላ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች በስፋት ሲንጸባረቁ ከነበሩ ጥያቄዎች መካከል የብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄ ዋነኛው ነው:: በዚህ ወቅት ውስጥ ለብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄ በፖለቲካ ኃይሎች የቀረቡት የመፍትሔ ሃሳቦች የተለያዩ ቢሆንም የመፍትሔ ሃሳቦቹ የሚመነጩት ግን በዋናነት ከሁለት ተገዳዳሪ አስተሳሰቦች ነው:: አንደኛው አስተሳሰብ የሚያጠነጥነው የብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄው የሚካትተው ከኢትዮጵያ ዘመናዊ የሃገር ግንባታ ጋር ተያይዞ የተፈፀሙ ታሪካዊ ኢ-ፍትሃዊነትንና በደሎችን እንዲሁም በያ ትውልድ ውስጥ የተፈፀሙ መጠፋፋትን አካቶ ሁሉን-አካታች መድረክ በማዘጋጀት ያለፈውን በደሎች ዕውቅና በመስጠት በፖለቲካ ሊህቃን መካከል መግባባትን ማስፈንን ነው:: ሁለተኛው አስተሳሰብ የብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄን የሚመለከተው ኢትዮጵያን እንደ ሀገር በአዲስ መሰረት ላይ የመገንባት ሂደት አድርጎ ነው:: ይህም ማለት የብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄ የሚያቅፈው ሁሉንም አይነት ማለትም ብሔር፣ ሃይማኖት እንዲሁም መደብ ላይ መሰረት ያደረገ ኢ-ፍትሃዊነትና መገለልን ከኢትዮጵያ ዘመናዊ የሃገር ግንባታ ጀምሮ የኢህአዴግን የአገዛዝንም የሚያካትት ነው::

በሁለቱ አስተሳሰቦች መካከል ያለው ልዩነቶች የሚከተሉት ናቸው:: የመጀመሪያው አስተሳሰብ ብሔራዊ ዕርቅን እንደ ፖለቲካዊ መፍትሔ ሲያይ፤ ሁለተኛው አስተሳሰብ ብሄራዊ ዕርቅን እንደ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ጉዳዮችን የሚያካትት እንደ ሁሉን አቀፍ የመፍትሔ ሃሳብ ነው:: በተጨማሪም፣ ብሔራዊ ዕርቅን እንደ ፖለቲካ መፍትሔ የሚያራምዱት በአብዛኛው እራሳቸውን <<የአንድነት ኃይሎች>> ብለው የሰየሙት የፖለቲካ ኃይሎች ሲሆኑ፤ብሔራዊ ዕርቅን እንደ-ሁሉን አቀፍ የመፍትሔ አቅጣጫ የሚያዩት በአብዛኛው ብሔር ላይ የተመሰረቱ ፖለቲካ የሚያራምዱ ኃይሎች ናቸው:: <በአንድት ኃይሎች> ውስጥም ቢሆን በሀገር ቤት የሚንቀሳቀሱት ኢህአዴግን እንደ አንድ የፖለቲካ ኃይል በብሔራዊ ዕርቅ ሂደት ውስጥ መሳተፍ እንደለበት ሲያመለክቱ(ዕርቅን ከፍትህ ሲያስቀድሙ)፤ከሀገር ውጭ የሚንቀሳቀሱት(ፍትህን ከዕርቅ የሚስቀድሙ ናቸው::) ግን ይህን አይደግፉም:: በብሔር ላይ የተመሰረቱትም ውስጥም ኢህአዴግ የብሔራዊ ዕርቅን አሁን ባለው <<ህገ መንግስት>> ላይ መግባባትን የመፍጥር ሂደት አድርጎ ሲመለከት (reconciliation as a means of defending the status quo)፣ በተቃዋሚነት ጎራ ውስጥ ያሉት ደግሞ የብሔራዊ ዕርቅ ሂደትን ባለፉት አገዛዞች (የኢህአዴግን ዘመንንም ይጨምራል) ለተፈጸመባቸው በደሎችና መገለሎች ዕውቅና የመስጠትንና ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍትሃዊነትን (reconciliation as an instrument to create and maintain a system of balance of power) እንደሚያሰፍን ሂደት አድርገው ይገልጹታል:: በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች የብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄ የሚያራምዱ ቢሆንም የብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄና አስፈላጊነቱ ላይ ተመሳሳይ ግንዛቤ የላቸውም:: ስለዚህም ሁሉም <የብሔራዊ ዕርቀ ጥያቄ> ቢያራምዱም ቃሉ ያዘለው የተለያዩ ትርጓሜዎች ከመሆኑም በላይ የተግባር እንቅስቃሴዎች ውጤታማ እንዳይሆኑ አድርጓል::

የዚህ ፁሁፍ አላማ ከላይ በተጠቀሱት የአስተሳሰብ ልዩነቶች ምክንያት የብሔራዊ እርቅ ከገባበት ቅርቃር (deadlock) ውስጥ የሚወጣበትንና በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲመሰረት ለምንፈልገው የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ እንደ አንድ ዋና ምሶሶ ጭምር የምንጠቀምበትን አግባብ ለመጠቆም ነው:: ስለዚህም፣ ይህ ጹሁፍ መጀመሪያ የብሔራዊ ዕርቅ ትርጓሜና አስፈላጊነት በአጭሩ ይዳስሳል፤ ቀጥሎም ለምን በኢትዮጵያ የብሔራዊ ዕርቅ አስፋላጊነት እንደሆነ ያመላክታል፣

በመቀጠል የብሔራዊ ዕርቅ ፈተናዎችና የመፍትሄ ሃሳቦችን ያስቀምጣል፤ በስተመጨረሻም የፅሁፉ ማጠቃለያ ሃሳብ ይቀርባል።

## 2. ብሄራዊ ዕርቅ ትርጓሜና አስፈላጊነቱ

በአንድ መህበረሰብ ውስጥ ጉልበትን መሰረት ያደረጉ የቅራኔ አፈታት ሂደቶች ከሚያስከትሏቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች በተጨማሪ ውድ የሆነውን የሰው ልጆች ህይወት መጥፋትን፣ በሰዎች ልቦናና ህሊና ውስጥ የበቀልና የጥላቻ ስሜትን ያስከትላሉ። ብሔራዊ ዕርቅም በሰው ልጆች ልብና አእምሮ ውስጥ የሰረጹትን የበቀልና የጥላቻ ስሜት የሚሻርበትና በምትኩ በሰላምና ፍቅር ላይ የተመሰረቱ ማህበረሰባዊ ግንኙነቶች እንዲያብቡ መንገድ የሚከፍት ነው። ምንም እንኳን የተለያዩ ምሁራኖች የተለያዩ ፍቺ ቢሰጡትም በአመዛኙ የሚስማሙበት ትርጓሜ- ብሔራዊ ዕርቅ ያለፈውን በደልና ጥላቻ እንዳይደገሙ የሚያረግግና የሁሉም የጋራ የሆነች አገርን የመገንባትና በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ሀገራዊ መግባባት መፍጠር ማለት ነው [i]።

የጋራ ነገን የመፍጠር ሂደት የሚመሰረተው ደግሞ ያለፍን የቁርሾ ማህበረሰባዊ ግንኙነት በመሻርና አዲስ አስተሳሰብና የጋራ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ ማህብረሰባዊ ግንኙነት ሲተካ ነው። ብሔራዊ ዕርቅ ሀገራዊ መግባባትን ከማስፍን፣ ያለፈን በጎ ያልሆነ ማህበረሰባዊ ክፍፍሎሽንና ታሪካዊ ኢ-ፍትሃዊነትን ከማስወገድ እንዲሁም ሁሉን አቀፍ እና ሁሉን የማህበረሰብ ክፍል ተጠቃሚነትን ያረጋገጠ ሀገራዊ አንድነትን ከመገንባት አንጻር ያለው ጠቃሚነት ጉልህ ነው [ii]።

ይኸም ማለት ብሔራዊ ዕርቅ የአጭር ጊዜ ፕሮጀክት ሳይሆን የራሱ የሆነ ሂደት ያለው ሆኖ ያለፉት በደሎችና ኢ-ፍትሃዊ የሆኑ ድርጊቶች ለመፈጸማቸው እውቅና መስጠትን (Acknowledgment)፣ የተፈጸሙትን በደሎች ያስከተሉት ውጤቶች ላይ፣ ተጎጂዎች የከፈሉት መስዋትነት እና እንድምታ ላይ ስምምነት መድረስን (Consensus building)፣ የተፈጸሙት በደሎች በድጋሚ እንዳይፈጸሙና የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ፍላጎትና ደህንነት የሚያረግገጥ ስርአት ለመፍጠር መዋቅራዊ ለውጦችን ማምጣትና የፖለቲካ ውህደትን ማሳለጥን (Structural changes and institutionalization of the process of political integration)፣ ፈጣን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት በማምጣት የኢኮኖሚያዊ ውህደትን ማረጋገጥና (enhancing socio-economic development and economic integration) እንዲሁም በባለፉት ስርአቶች የተገለሉትን የማህበረሰብ ክፍሎች ይበለጥ ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻልን የሚጠይቅ ነው [iii]።

ስለዚህም፣ የብሔራዊ ዕርቅ ስኬታማነትም ሆነ ዘላቂነት የሚወሰነው ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች መሟላት አለሟሟላት ላይ ነው። በመሆኑም ብሔራዊ ዕርቅ በራሱ እንደ ውጤት የሚታይ ነው። ብሔራዊ ዕርቅን ከዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ጋር አያይዞን ካየነው፤ ብሔራዊ ዕርቅ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ እንደ ግብአትም የሚታይ ነው [iv]። በአንባገነናዊ ስርአቶች ውስጥ ስርአቶቹ ከሚፈቅዷቸው ውጭ ያሉ ተጻራሪ ፍላጎቶችና ጥቅሞችን ለማዳፈን ጉልበትን መሰረት ያደረገ አካሄድ ይከተላሉ። ዴሞክራሲያዊ ስርአቶች ከአምባገነን ስርአቶች የሚለዩበት ዋናው ቁም ነገር ተጻራሪ ፍላጎቶችንና ጥቅሞችን ከጉልበት ነጻ በመሆነ መንገድ የማመቻመች (compromise) እና ተቋማዊ ገጽታ በማላበስ (institutionalization of conflicts) ስርአት አልበኝነትና ግጭቶች እንዳይፈጠሩ መድረግ መቻላቸው ነው። ይኸም ማለት አንባገነናዊ አገዛዞች ልዩነቶችን የሚያስተናግዱበት መንገድ አንዱን ወገን ተጠቃሚ አንዱን ደግሞ አግላይ ያደረገ ስለሚሆን በማህበረሰቡ ውስጥ የአሸናፊና የተሸናፊን ስነ-ልቦና የሚፈጥር ነው። አሸናፊው ቡድን አሸናፊ ሆኖ የሚቀየው የራሱን አቅም በቀጣይነት በመገንባትና ተሸናፊውን ይበልጥ አቅመ-ቢስ ለማድረግ በሚደረገው ትግል ውጤታማነት ልክ ነው። ተሸናፊው ቡድንም ተሸናፊ ሆኖ የሚቆየው የራሱን አቅም በመገንባትና የአሸናፊውን አቅም በማዳከም ተገዳዳሪ

ኃይል እስኪሆን ድረስ ነው:: በመሆኑም በአምባገነን ስርአቶች ውስጥ የሚፈጠሩት የማህበረሰባዊ ግንኙነቶች ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ምቹ ያልሆኑ ናቸው::

በዴሞክራሲያዊ ስርአቶች ውስጥ ግን ሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች ያሏቸውን ፍላጎቶችና ጥያቄዎቻቸውን የሚዳኙባቸውን ህጎችና አግባቦች በስምምነት(ሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች ወይም አብዛኛው ክፍሎች) የሚያጸድቋቸው በመሆኑ ለነዚህ ህጎችና አግባቦች እንዲሁም እነዚህን ህጎችና አግባቦች ተፈጻሚ ለሚያደርጉ ተቋሞች ስር ለመዳኘት የውዴታ ግዴታ የሚገቡበት ነው[v]:: ብሔራቂ ዕርቅም ባለፉት የአንባገነናዊ የአገዛዝ ስርአቶች የተፈጠሩ ኢ-ፍትሃዊ ድርጊቶችና በደሎች ያስከተሉትን በጎ ያልሆነ ማህበረሰባዊ ክፍፍሎሽ እና አንዱን የማህበረሰብ ክፍል ጠቃሚ ሌላውን ጎጂ (win-lose) ያደረገውን የፖለቲካ ባህል በመሻር ሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች አሸናፊና ተጠቃሚ የሚያደርግ (win-win) ፖለቲካዊ ባህል ለመገንባት አስተጽኦው ከፍተኛ ነው:: ስለዚህም፣ ብሔራዊ ዕርቅ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደት መሳካት ከሚጫወተው ሚና አንጻር እንደ አንድ ወሰኝ ምሶሶ የሚታይ ነው::

## 3. በኢትዮጵያ የብሔራዊ ዕርቅ አስፈላጊነት

በኢትዮጵያ ውስጥ ብሔራዊ ዕርቅ የሚስፈልግበት ምክንያቶችን በ ሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል:: እነርሱም:-

### ሀ) በኢትዮጵያ የሀገር ምስረታ ሂደት ውስጥ የተፈጠሩ የተዛቡ ግንኙነቶችን ለማረም

የኢትዮጵያ ታሪክ እንደ ሌሎች ሀገሮች ታሪክ ለታሪክ ምሁራንና ተመራማሪዎች የተተወ ሳይሆን የፖለቲካ አቋሞች የሚያዝበት ጉዳይ ነው:: ከአጼ ቴዎድሮስ የዘመናዊ መንግስት ምስረታ እንቅስቃሴ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ የተነሱ የፖለቲካ ልዩነቶችና የፍላጎቶች ግጭቶች በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ሊፈቱ የተሞከሩት ጉልበትን መሰረት ባደረገ የአፈታት ዘዴ ነው:: በዚህም የተነሳ ችግሮች እየተንከባለሉ ሳይፈቱ በመቅረታቸው ውስብስብና በጣም ስር እንዲሰዱ ሆነዋል:: በሌላ በኩል ደግሞ የዘመናዊት ኢትዮጵያ ሀገር ምስረታ ሂደት ፖለቲካዊው እንድምታው ያልተማከለና በጣም ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት መመስረት ሲሆን፣ ኢኮኖሚያዊው እንድምታው ደግሞ በጦር አሸናፊ ሆነው የማዕከላዊ መንግስት ምስረታን ሂደት የተቆጣጠሩትን ኃይሎች የኢኮኖሚ ጥቅሞችን የማስከበር ሂደት ነበር [vi]:: ይህ የሀገር ምስረታ ሂደት በመሰረቱ ሁለት አይነት ልሂቃንን ፈጥሯል:: አንደኛው የልሂቃን ክፍል እራሱን እንደ ‹ሀገር አቅኚ› እና ‹የዘመናዊ ስልጣኔ ምንጭ› ሲቆጥር ሁለተኛው የልሂቃን ክፍል ደግሞ እራሱን ‹ኢኮኖሚያዊ መሰረቱን› እንደተነጠቀና እና ከፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ስልጣን እንደተገፋ የሚቆጥር ነው:: ስለዚህም፣ በዘመናዊ የኢትዮጵያ ሀገር አመሰራረት ሂደት ላይ ተቀራራቢ የሆነ አረዳድ በተለያዩ ልሂቃን ውስጥ የለም:: እነዚህ ልሂቃኖች የሚያራምዱት ፖለቲካና በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲገነባ የሚፈልጉት ዴሞክራሲያዊ ስርአት መነሻ ምንጩ ባላቸው የዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ አረዳድ ነው::

ይህ የልሂቃኖቻችን የዴሞክራሲ አረዳድ በመሰረቱ ለዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ያላቸው አረዳድ ነጸብራቅ ነው:: የዘመናዊት ኢትዮጵያ የሀገር ምስረታ ሂደት በጦርነትና በማስገበር የታጀበ ነው:: ምንም እንኳን በኢትዮጵያም እንደሆነው ሁሉ በተወሰነ መልኩ ሁሉም ሀገሮች ሲመሰረቱ ጉልበትን መሰረት ያደረገ አካሄድ ቢጠቀሙም፤ የኢትዮጵያ የሀገር ምስረታ ፕሮጀክት ሲያልቅ የተተከለው የአገዛዝ ስርአት ግን ሄዶ ሄዶ ፍጹም ግለሰባዊ አገዛዝንና ሁሉን አካታች ያልሆነ ማህበረሰዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ስርአቶችን ወልዷል:: ስለዚህም የሀገር ምስረታ ሂደት በተለያዩ ልሂቃን መሀካል ቁርሾ ላይ ባስ ሲልም ጥላቻ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንዲኖር አስችሏል:: ይህ ‹እኛ-እነርሱ› አስተሳሰብ ዛሬም ቢሆን በፖለቲካ ልሂቃኖቻችን ውስጥ በስፋት የሚታይ ነው:: ስለዚህም ይህንን ጥላቻ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት በብሔራዊ ዕርቅ ሂደት አድሶ የጋራ የሆነች አገርን ለመገንባት በሚደረገው ሂደት ውስጥ ሁሉም የማህበረሰቦች ክፍሎች አተዋጽኦ

እስካላደረጉ ድረስ የተሻለ ብሩህ ቀንና ዴሞክራሲያዊት የሆነች ኢትዮጵያ ሊፈጠሩ አይችሉም። ለዚህም አላማ ሲባል ብሔራዊ ዕርቅ በጣም አስፈላጊ ነው።

የአገራችን ፖለቲካዊ ባህል ጉልበት ላይ የተመሰረተ ነው። አጼ ቴዎድሮስ የነጉሰ ነገስትነት ዙፋን ላይ የተቀመጡት በጠበንጃ ኃይል ሁሉንም ተገዳዳሪዎቻቸውን በማንበርከክ ነው። አጼ ዮሃንስ፣ አጼ ሚኒሊክ፣ አጼ ኃይለ ስላሴ የንጉሰ-ነገስትነት ዙፋኑን የተቆጣጠሩት ከተገዳዳሪዎቻቸው በወታደራዊ ኃይል በተነጻጻሪነት በልጠው ስለተገኙ ነው። ፕሬዘዳንት መንግስቱ  ሆነ ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ የፖለቲካ ስልጣኑን ቆንጮ ቦታ የተቆጣጠሩት በጠበንጃ ኃይል ታግዘው ነው። ይህ ጉልበትን መሰረት ያደረገ የስልጣን ዝውውር በመሰረቱ በጊዜ ሂደት የሚፈጥረው የፖለቲካ ባህል ሁሉን አካታች የሆነ የአስተዳደር ስርአት ለመዘርጋት አመቺ የሆነ ስነ-ልቦናን አይደለም። የኛ የፖለቲካ ባህል የጠበንጃ የፖለቲካ ባህል ነው። ለዚህም ነው ትናንሽ ልዮነቶቻችን ሳይቀር አጉልተን በማውጣት ሊያስተባብሩን የሚችሉትን አያሌ ነገሮች ወደ ጎን በመግፋት ለእርስ-በእርስ መጠላለፍ ቅርብ የሆነው። ይህ አካሔድ የሚፈጥረው ነገር ቢሆር ሁሉም የየራሱን ትናንሽ ገነት የማደራጀት አካሄድን እንጂ በትልቁ ሊያስተሳስረን የሚችልን አካሄድ አይደለም። በተወሰነ መልኩም ቢሆን ከ 73 በላይ በሀገር ቤት የተመዘገቡ ትናንሽ የፖለቲካ ፓርቲዎች መኖራቸው የሚያመላክተው ቁም ነገር ይሄንኑ እውነታ ነው። ይህ ትናንሽ ገነቶችን የመፍጠር ሂደት የሀገራችንን የፖለቲካ ዕድገት ወደ ፊት አንድ እርምጃ ከማራመድ አንጻር ምን አስተዋጽኦ አደረገልን? ይህንን በጉልበት ላይ እና የራስን ፍላጎት ብቻ በማየት የሌሎቹን የፖለቲካ ኃይሎች ህልውናን የመካድ ባህልን ለማስወገድና በመተባበርና በተወሰነ መልኩም ቢሆን በመተማመን ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ ባህል ከመፍጠር አንጻር ብሔራዊ ዕርቅ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

## ለ) በአገዛዞችና በሀይማኖቶች መካከል የተዛባ ግንኙነቶችን ለማስተካከል

የዘመናዊት ኢትዮጵያ ምሰረታ የተመራው <አንድ ሀገር፣ አንድ ኃይማኖት> በሚለው መርህ ነው። ምንም እንኳን ኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖትን ከተቀበሉት ሀገሮች ቀደምት ብትሆንም፣ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የነበራቸው ሚና በጣም ዝቅተኛ ነበር። ይህ የሙስሊም ኢትዮጵያውያን ሚናን እንዲቀጭጭ ያደረገው ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ መንግስታዊ ሃይማኖት መኖሩና በዚህም ምክንያት ሙስሊሞች በፖለቲካው መስክ እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንዲቆጠሩ ስለሆኑ ነው። የአጼ ኃይለ ስላሴ የአገዛዝ ዘመን ማክተም ሁለት አበይት ክስተቶችን አስከትሏል። አንደኛው መንግስታዊ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ማክተሙ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የእስልምናን ሃይማኖታዊ በዓላት ብሔራዊ በዓላት በማድረግ በሀገረ-አቀፍ ደረጃ መከበር መጀመሩ ነው። ሆኖም ግን በደርግ-ዘመነ መንግስትም ሆነ በኢህአዴግ አገዛዝ ሙስሊም ኢትዮጵያውን ከሁለተኛ የዜግነት ደረጃ ወደ እኩል የዜግነት ደረጃ የማምጣቱ ሂደት ግን እምብዛም ግቡን አልመታም[vii]።

ይልቁንም ኢትዮጵያ ከምትገኝበት ጂኦ-ፖለቲካዊ ሁኔታ፣ ከኢህአዴግ መንግስት መሰረታዊ ባህሪና ኢትዮጵያ ተሳታፊ ከሆነችበት አሜሪካ መራሹ አለም አቀፍ የጸረ-ሽብርተኝነት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ የመግባትና ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎችን የመቆጣጠር ሂደት በተወሰነ መልኩ በሀገሪቱ ውስጥ አክራሪነት እንዲስፋፋ አድርጓል። እዛም እዚ በተወሰኑ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችና በክርስቲያን በተለይ ደግሞ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል እየተፈጠሩ ያሉ ግጭቶች የሚያመላክቱት ነገር በሃይማኖት ላይ የተመሰረተ ግጭቶች እየተስፋፉ መሆናቸውን ነው። እነዚህ እየተስፋፉ ያሉ ግጭቶች <<በመቻቻል>> ላይ የተመሰረተ የሃይማኖታዊ ግንኙነቶች እሴቶች እየተሸረሸሩ ስለመሄዳቸው የሚጠቁሙ ናቸው [viii]።

በሌላም በኩል ደግሞ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ የሆነና የሁሉን የማህበረሰብ ክፍሎች ፍላጎቶች ያማከለ አገዛዝ የለም ካልን፣ የሙስሊሞችን እንደ አንድ የማህበረሰብ ክፍል ሃይማኖታዊ ነጻነትን የሚያከብርም ሆነ ማህበረሰባዊ

ፍላጎቶችንና ጥያቄዎች የሚመለስ የአገዛዝ ስርአት አልነበረም ማለት ነው። ይህም ማለት በህዘበ-ክርስቲያኑና በህዘበ-ሙስሊሙ መሀከል ያለው <<በመቻቻል>> ላይ የተመሰረተ ግንኙነት የአገዛዝ ስርአቱን በሚያራምዱት ጥቂት ልሂቃን ምክንያት ሊበረዝ የሚችልበት አጋጣሚ ከፍተኛ ይሆናል። ምክንያቱም፣ በቀላሉ የእስልምና አክራሪነትን የሚያራምዱ ኃይሎች የሀገሪቱን ስልጣን በተቆጣጠሩትና በህዝቡ መካከል ያሉ ግንኙነቶች (state-society relationships) የአገዛዝ ልሂቃኑን ማህበረሰባዊ መደብ በመውሰድ እንደ ሃይማኖት ላይ የተመሰረተ የጨቋኝ-ተጨቋኝ ግንኙነቶች ሊተረጉማቸው ይችላሉ። ስለዚህም፣ በታሪካዊ አጋጣሚም ሆነ በፖለቲካዊ ምክንያት የተፈጠሩ በሀገሪቱ ለረጅም ዘመን ዘልቆ የቆየውን <<በመቻቻል>> ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ለማስቀጠልና ተቋማዊ ገጽታ ሰጥቶ ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ ብሔራዊ ዕርቅ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

## ሐ) በፖለቲካ ሊህቃኖች መካል በጥላቻ ላይ የተመሰረተ ግንኙነትን ለማስወገድ

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባህል ጠበንጃ ላይ የተመሰረተ ፓለቲካ ባህል ነው ካልን፣ ይህ ባህል የሚወልዳቸው በጥላቻና እርስ በእርስ ህልውናን በመካካድ ላይ የተመሰረተ ግንኙነቶች መኖራቸው የማይቀር ሃቅ ነው። እነዚህ ግንኙነቶች አንድም በተለያዩ ልሂቃኖች ውስጥ የተዛባ ግንኙነቶች እንዲስፋፉ ሲያረጉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ ልሂቃኖቻችን የጋራ ጥቅምን የሚያስከብርንና በመተባበር ላይ የተመሰረተ ህብረትን መመስረት እንዳይችሉ አርጓቸዋል። ለዚህም ትልቁ ምሳሌ፣ በአንድ በኩል በኢትዮጵያ የመጀመሪዎቹ ፖለቲካ ፓርቲዎች (ኢህአፓ እና መኢሶን) መሀከል ከነበረው  እርስ በእርስ የመጠፋፋት ፖለቲካ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ልዩነቶችን ሰላማዊ መንገድ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ በመሆን በመነጋገር የፈቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሉንም። ጨካ የነበሩት ልዩነታቸውን የፈቱት በተለመደው በጠበንጃ ነው፤ ከተማ ውስጥ ያሉትም ቢሆን ስም በመጠፋፋት፣ እርስ በእርስ እቅውና በመነሳሳትና አልፎ አልፎም በመደባደብ ነው የፈቱት አሊያም ደግሞ ለመፍታት እየሞከሩ ያሉት።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የተሞከሩት ጥምረቶች፣ መድረኮች፣ ቅንጅቶች እና በአጠቃላይ ስብስቦች ውጤታማ ያልሆኑበት የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም፤ በዋናነት ግን እነዚህ ስብስቦች የተመሰረቱበት ችግሮች መሰረታዊ ስህተት ስላለበት ነው። ስብስቦቹ የተቋቋሙበት መሪ መርህ <<ፖለቲካ ፓርቲዎች ለየብቻ ገዢውን ፓርቲ መቋቋምና መገዳደር (<አንድ-ለአንድ>) አንችልም፣ ተሰባስበን (<አንድ-ለብዙ>) ገዢውን ፓርቲ ከስልጣን እናውረደው>> የሚል ነው። ይህ መርህ በመሰረቱ ፖለቲካ ፓርቲዎች ያሏቸውን ልዩነቶች በማጥበብ የተሻለ ብሩህ ቀን ለመፍጠር የሚያደርጉት አካል ሳይሆን (ስብስቦቹ ያወጧቸውን መለስተኛ-ማኒፌስቶዎችና የየፓርቲዎቹን የፖለቲካ ፕሮግራም በመሰረታዊ የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ ያላቸው መልሶች ምን ያህል እንደሚራራቅ ልብ ይሏል)፣ <ትልቁ ጠላት> የሚሉትን ገዢውን ፓርቲ በጋራ ከስልጣን በማውረድ ከዛ በኋላ ደግሞ እርስ በእርስ በመጠላለፍ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት የሚቆምሩት ፖለቲካዊ አካሄድ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ የተፈጠሩ ስብስቦች ሲፈርሱ የፈጠሩት ትልቁ ፖለቲካዊ ጠባሳ በፖለቲካ ኃይሎች መካከል የጥላቻ፣ የቂም በቀልና እርስ በእርስ የመጠራጠር ባህል ይበልጥ ስር እንዲሰድ ማድረጋቸው ነው።

ስለዚህም፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉንም አካታች የሆነ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመፍጠር እና ፍትሃዊ-ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን በማስፈን የተሻለ ነገን ለመፍጠር፣ የግዴታ ከአገዛዝ ለውጥ (Regime change) በላይ የሆነ ማህበረሰባዊ ለውጥ ማምጣት ይጠበቅብናል። በማህበረሰባችን ውስጥ የተፈጸሙ ታሪካዊ ኢ-ፍትሃዊነቶችንና በደሎችን እንዳይደገሙ ለማድረግ፣ በሃይማኖቶች መካከል እየተስፋፉ የመጣው ያለመቻቻል ባህልና ለመቀነስ እና በፖለቲካ ልሂቃኖቻችን መካከል ጠልፎ የመጣል የግለኝነት ፖለቲካን ለማስወገድ ብሔራዊ ዕርቅን እንደትልቅ የመፍትሄ ቁልፍ መውሰድ ይገባናል።  ብሔራዊ ዕርቅን በፖለቲካ ሊህቃኖች መካከል ያሉትን ቁርሾዎች ብቻ ለመሻር ሳይሆን ማህበረሰባዊ ለውጥን

ለማምጣት ጭምር መጠቀም አማራጭ የሌለው አካሄድ ነው። ሆኖም ግን፣ ብሔራዊ ዕርቅን ለማስፈን የተጋረጡ ብዙ ፈተናዎች በአገራችን ውስጥ አሉ። እነዚህ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው? የመፍትሄ አቅጣጫዎቹስ?

ክፍል ሁለት ይቀጥላል።

---

[i] Bloomfield, David, Teresa Barnes, and Lucien Huyse. 2003. *Reconciliation After violent conflict: A Handbook*. Stockholm: Interna-tional IDEA.

[ii] Lederach, John Paul. 1997. *Building Peace: Sustainable Reconciliation in Divided Societies*. Washington, D.C. : United States Institute of Peace.

[iii] Solimano, Andres (Ed.). 2000. *Colombia: Essays on Conflict, Peace and Development*. Washington, D.C., The World Bank.

[iv] Liebenberg, Ian and Abebe Zegeye. 1998. "Pathway to Democracy? The Case of the South African Truth and Reconciliation Process." *Social Identities*, Volume 4, Number 3, pp. 541-558.

[v] Diamnond, Larry. 2008. *The Spirit of Democracy: The Struggle to Build Free Societies Throughout the World*. New York, Henry Holt and Company, LLc,.

[vi] Bahru Zewde. 2005. *A History of Modern Ethiopia, 1855-1991*. Ohio: Ohio University Press. 2nd Edition.

[vii] Dereje Feyissa. 2013."Muslims Struggle for Recognition in Contemporary Ethiopia". In *Muslim Ethiopia: The Christian Legacy, Identity Politics and Islamic Reformism*, eds. Patrick Desplat and Terje Østebø. New York, Palgrave Macmillan.

[viii] Desplat, Patrick; Terje *Østebø* . 2013. "Muslims in Ethiopia: The Christian Legacy, Identity Politics, and Islamic Reformism". In *Muslim Ethiopia: The Christian Legacy, Identity Politics and Islamic Reformism*, eds. Patrick Desplat and Terje Østebø. New York, Palgrave Macmillan.